# ክልላዊ ማደንዘዣ ለሲዘርያን ቀዶ ጥገና

## የአከርካሪ እና ኢፒዱራል ማደንዘዣ

### ክልላዊ ማደንዘዣ ምንድን ነው?

ክልላዊ ማደንዘዣ በአንድ የሰውነትዎ ክፍል ውስጥ ህመም እንዳይሰማዎ የሚከላከል መድሃኒት ነው።

በቀዶ ጥገና ሲዘሪያ ወቅት ህመም ሳይሰማዎም ልጅዎ ሲወለድ ነቅተው እንዲቆዩ ያስችላል። ይህ ደግሞ በቀዶ ህክምና ወቅት እንቅልፍ እንዲተኙ ከሚያስችልዎት አጠቃላይ ማደንዘዣ ጋር አንድ አይደለም።

ክልላዊ ማደንዘዣ በሁለት ዘዴዎች ሊሰጥ ይቻላል።

- በጀርባዎ ውስጥ ባሉ አጥንቶች መካከል እንደ አንድ መርፌ ይሰጣል – ይህ የአከርካሪ ማደንዘዣ ነው።
- በጀርባዎ ውስጥ በተቀመጠ አነስተኛ የፕላስቲክ ቱቦ አማካኝነት – ይህ ኤፒዱራል ማደንዘዣ ነው።

ሁለቱም ዓይነት ማደንዘዣዎት የህመም መልእክቶች በነርቮችዎ ውስጥ እንዳይተላለፉ ይከላከላሉ።

ከደረትዎ ወደ ታች ያለው አካል ይደነዛል፤ ስለሆነም እግሮችዎን ማንቀሳቀስ አይችሉም።

ክልላዊ ማደንዘዣ በቀዶ ጥገና ሲዘሪያ ለሚወልዱ የሚሰጥ በጣም የተለመደ የማደንዘዣ ዘዴ ነው።

### ጥቅሞቹ ምንድን ናቸው?

ከአጠቃላይ ማደንዘዣ ጋር ሲነጻጸር የክልል ማደንዘዣ:

- በአብዛኛው ለርስዎ ይበልጥ አስተማማኝ ነው።
- ልጅዎ ሲወለድ ንቁ እንዲሆኑ ያስችልዎታል።
- ከቀዶ ጥገና ህክምና በኋላ ለብዙ ሰዓታት የተሻለ የህመም ማስታገሻ ይሆናል፤ መርፌ መወጋት (ሞርፊን) ሲጨመር ደግሞ የህመም ማስታገሻው እስከ 24 ሰዓት ሊዘልቅ ይችላል።
- የእንቅልፍ ድካምዎን ይቀንሳል
- ልጅዎን ከወለዱ በኋላ ቀደም ብለው ለማቀፍና ለመመገብ ያስችልዎታል
- አብዛኛውን ጊዜ የትዳር ጓደኛዎ ወይም ድጋፍ ሰጪዎ በሚወልዱበት ጊዜ አብሮ እንዲኖር ያስችላል፤ ይህንን ጥቅም ደግሞ አጠቃላይ ማደንዘዣ አይሰጥም።

### ሊከትሉ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ወይም አደጋዎች ምንድን ናቸው?

ክልላዊ ማደንዘዣ ሲወስዱ:

- በቀዶ ጥገና ህክምናው ወቅት በሆድ አካባቢ የተወሰነ እንቅስቃሴ፣ የመጎተት ስሜት እና ግፊት ሊያጋጥምዎ ቢችልም ምንም ዓይነት ህመም አይሰማዎትም።
- መርፌውን ከተወጉ በኋላ ከ2 እስከ 4 ሰዓት ድረስ እግሮችዎን ማንቀሳቀስ እንደማይችሉ ነው።

ክልላዊ ማደንዘዣ ተጨማሪ የጎንዮሽ ጉዳት ወይም አደጋ ሊያስከትል ይችላል። የማደንዘዣ መድሃኒት ከወሰዱ በኋላ የሆነ ችግር ወይም ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምልክቶች መካከል አንዱ ካለብዎ ከእርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ ጋር መነጋገር።

ከተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ጋር የሚካተት:

- የደም ግፊት መቀነስ። ይህ ደግሞ የመደንዘዝ ስሜት፤ በራስህ ላይ ብርሃን ማሳደር ወይም የመታመም ስሜት እንዲያድርብዎ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ሁኔታ የሚከሰተው የአከርካሪ አጥንት ማደንዘዣ ከወሰዱት 2 ግለሰቦች መካከል አንዱ ሲሆን እንዲሁም ከ20 ግለሰቦች መካከል አንዱ ደግሞ የኤፒዶራል ማደንዘዣ መውሰድ ይሆናል።
- ከ20 ሰዎች መካከል በአንዱ ላይ የመንቀጠቀጥ ወይም ምሳከክ ችግር ሊያስከትል ይችላል።
- ከኤፒዱራል ማደንዘዣ ጋር ከ8 እስከ 10 ከሚደርሱ ሰዎች መካከል አንዱ ተጨማሪ የአካባቢ ማደንዘዣ ያስፈልጋል ወይም በጀርባቸው ላይ ያለው ቱቦ ውስጥ መፈተሽ ወይም መተካት ሊያስፈልግ ይችላል።

ራስ ምታት እምብዛም አይከሰትም። የኤፒዱራል ማደንዘዣ ከወሰዱት ከ100 ግለሰቦች መካከል በአንዱ ላይ እንዲሁም የአከርካሪ አጥንት ማደንዘዣ ከወሰዱት ከ200 ግለሰቦች ደግሞ በአንዱ ላይ ችግር ይፈጠራል።

በጣም አነስተኛ ከሆኑት ችግር ፈጠራ ለሚከተሉት ያካትታል:

- የነርቭ ጉዳት (እንደ በታፋ እግር ወይም በታችኛው እግር ላይ መደንዘዝ ወይም ድካም)፣ የአከርካሪ ብክለት ኢንፌክሽን ወይም ማኔንጅተስ እንዲሁም ያልተጠበቀ ማደንዘዣ ስሜት መሰራጨት (በአከርካሪ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ማደንዘዣ በሸን ውስጥ ከገባ) ጉዳቱ ሊደርስ ይችላል።

ከባድ ጉዳት ወይም ሽባነት በጣም ያልተለመደ ነገር ነው።

## ይህ የሚሰጠው እንዴት ነው?

ክልላዊ ማደንዘዣ መድሃኒት የሚሰጠው በማደንዘዣ ባለሙያ ሀኪም በኩል ነው።

ትንሽ የፕላስቲክ ቱቦ (ካኑላ/cannula) በእጅዎ ወይም በክንድዎ ላይ ባለ ቬን ውስጥ ይገባና እንዲሁም በቧንቧ አማካኝነት ጠብ ጠብ እያለ ፈሳሾችን ያገኛሉ። የደም ግፊትዎና የልብ ትርታ መጠን ክትትል ይደረግለታል።

ሰውነትዎ ትክክለኛ ቦታ እንዲይዝ ይታገዛሉ። ቁጭ ብለው ይሁን ቀጥ ብለው ተቀመጠው ልጁን እጥፍ ብለው እንዲያቅፉት ይታገዛሉ።

የእርስዎን ታችኛውን ጀርባ በአንቲሴፕቲክ ቅልቅል ይጸዳል። ።

የማደንዘዣ ባለሙያው በጀርባዎ ያሉትን አጥንቶች ይመረምራል። የአካባቢ ማደንዘዣ መርፌ በቆዳዎ ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን ይህም እንዲደነዝዝ ያደርገዋል።

መርፌው በሚገባበት ጊዜ በጀርባዎ አካባቢ የግፊት ስሜት ይኖርብዎታል። በአሰራር ሂደቱ ቀጥ ብሎ መቆየቱ የቀዶ ጥገናው ህክምና በተሳካ ሁኔታ እንዲቀጥልና የነንዮሽ ጉዳት ሊያስከትል የሚችለውን አጋጣሚ ለመቀነስ ይረዳል።

- ለኤፒዱራል፤ ትንሽ የፕላስቲክ ቱቦ ወደ ጀርባዎ ይገባል። ይህም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ማደንዘዣ ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል።
- ለአንድ የአከርካሪ ቀዶ ጥገና ህክምና አንድ ዓይነት አካባቢ የሚያደነዝዝ መድሃኒት ይወጋሉ። ልጅዎን እስኪወልዱ ድረስ ለሚካሄድ ቀዶ ጥገና ድረስ ለሚያክል ጊዜ መስራት አለበት።

መርፌው ይወጣና በጀርባዎ ላይ ይተኛሉ። ትንሽ ወደ ግራ ዘንበል ብለው።

የማደንዘዣው መድሃኒት ሥራ የሚጀምረው ከ5 እስከ 20 ደቂቃ ባለው ጊዜ ነው። ቀዶ ጥገና ህክምናው ከመጀመሩ በፊት የማደንዘዣ ባለሙያው ስለመደንዘዝዎ ያረጋግጣል፤ አብዛኛውን ጊዜ በበረዶ ላስቲክ  አማካኝነት እንደደነዘዙ ያረጋግጣል።

የማደንዘዣ ባለሙያ ሀኪሙ በተቻለ መጠን ምቾት እንዲሰማዎትለማድረግ የቀዶ ጥገና ህክምናውን በሙሉ ጊዜ አብሮዎች ይቆያል።

## ሌሎች የማደንዘዣ መድሃኒት አማራጮች የትኞቹ ናቸው?

በምጥ ወቅት ለህመም ማስታገሻ የሚሆን ኤፒዱሪያል ከተሰጥዎት፤ በኤፒዱራል ካቴተር አማካኝነት ማደንዘዣ መድሃኒት ማግኘት ይችላሉ።

ይህም ከአከርካሪ ማደንዘዣ ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የህመም እፎይታ ይሰጣል። ለበለጠ መረጃ ለምጥ የኤፒዱራል ህመም ማስታገሻ የሚለውን ሓቃዊ ጽሁፍ ያንብቡ።

ሌላው አማራጭ ደግሞ አጠቃላይ ማደንዘዣ ሲሆን ይህም ልጅዎ በሚወለድበት ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ይተኛሉ ማለት ነው። አጠቃላይ ማደንዘዣ የወሰዱ እንደሆኑ፤ የትዳር ጓደኛዎ ወይም ድጋፍ ሰጪዎ በቀዶ ጥገና ህክምና ክፍል ውስጥ መግባት አይፈቀድላቸውም፤ እንዲሁም በማደንዘዣ መድሃኒት ምክንያት ልጅዎ እንቅልፍ ሊወስደው ይችላል።

## ለበለጠ መረጃ

ስለ ክልላዊ ማደንዘዣ ጥያቄዎች ካልዎት የማደንዘዣ ባለሙያን መጠየቅ ወይም የቀዶ ጥገና ህክምና በሚደረግበት ቀን ስላለዎት አማራጮች መወያየት ይችላሉ።

ቀዶ ጥገና ህክምና ከማድረግዎ በፊት ጥያቄዎችን መጠየቅ ወይም ስላለዎት አማራጮች መወያየት ከፈለጉ የማዋለድ ህክምና  ባለሙያ ወይም አዋላጅዎንማናገር ይችላሉ። ከአንድ የማደንዘዣ ባለሙያ ጋር እንዲነጋገሩ ሊያቀናጅልዎ ይችላል።

**አጣዳፊ የህመም አገልግሎት/Acute Pain Service, The Royal Women's Hospital**

ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ  8 ሰዓት (am) እስከ ከሰዓት በኋላ 4 (pm)
ስልክ: (03) 8345 2389

## አስተርጓሚ ይፈልጋሉን?

ካስፈለግዎ አስተርጓሚ እንዲቀርብ መጠየቅ ይችላሉ።

## በቤተሰብ ሁከት ፈጠራ ድጋፍ

**1800 Respect National Helpline**

የጾታ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ወይም በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።
ቀን ወይም ማታ በማንኛውም ጊዜ መደወል ይችላሉ።

1800 737 732  1800respect.org.au

**የእኔ ኣይደለም ስለማለት/Disclaimer:** ይህ ሓቃዊ ጽሁፋዊ ወረቀት አጠቃላይ መረጃ ብቻ ያቀርባል። ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የጤና እንክብካቤ በተመለከተ ግልጽ የሆነ ምክር ለማግኘት ከጤና ባለሞያዎችዎ ምክር መጠየቅ ይኖርብዎታል። ሮያል የሴቶች ሆስፒታል የጤና ባለሙያ ከማየት ይልቅ በዚህ ሓቃዊ ጽሁፍ ወረቀት ላይ በመመካትዎ ምክንያት ለሚደርስብዎት ኪሳራ ወይም ጉዳት ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይቀበልም። እርስዎም ሆኑ ልጅዎ አጣዳፊ የሆነ ህክምና እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እባክዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ህክምና ክፍል ያነጋግሩ።
© The Royal Women's Hospital 2025